በሚቀጥለው ወር ግንቦት 15 2002 የሚደረገውን የይስሙላ ምርጫ በሚመለከት ከኢትዮጵያ የተቃዋሚ ድርጅቶች የተሰጠ የጋራ መግለጫ

## ነጻና ፍትሓዊ ምርጫ ሕገ-ወጥና አምባገነናዊ በሆነው የወያኔ ስርአት ስር ከቶውኑ ሊከናወን አይችልም

የኢትዮጵያ ህዝብና የወያኔን አምባገነናዊ አገዛዝ የሚቃወሙ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ድርጅቶች ከ1997ቱ ምርጫ መጭበርበር ዓብይ ትምህርት ተምረዋል። ይህ ትምህርት ከፍተኛ የህይወት መስዋእትነት የተከፈለበት ስለሆነ በቀላሉ ሊዘነጋ አይገባም። ይህ ትምህርት ደግሞ ነጻና ፍትሓዊ ምርጫ እንዲደረግ፣ ብሎም በምርጫ ህዝብ ለፈቀደው የፖለቲካ ድርጅት የሰጠው ድምጽ እንዲከበር፣ የወያኔ አገዛዝ ባለፈው ምርጫ የህዝብን ድምጽ ለመዝረፍ የተጠቀመባቸው መንግስታዊ ተቋማት በሙሉ ከወያኔ አምባገነናዊ አገዛዝ ቁጥጥር ውጭ መሆን እንደሚገባቸው ያረጋገጠ ነው። እነዚህ ተቋማት ሁሉንም ህዝብና የፖለቲካ ድርጅቶች በገለልተኛነትና በእኩልነት ማስተናገድ እንዲችሉ ሆነው መደራጀት የሚገባቸው መሆኑን ያመለከተ ትምህርት ነው። እነዚህ ከወያኔ ቁጥጥር ውጭ መደራጀት የሚገባቸው ወሳኝ ተቋማት፦

1. ከወያኔ ድርጅትና ወደፊትም ቢሆን ከሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች ጉዳይ አስፈጻሚነት ነጻ የሆነ የመከላከያ፣ የደህንነትና የፖሊስ ሃይል

2. ነጻ የፍትህ ስርአት

3. ነጻ የምርጫ አስፈጻሚ ቦርድ

4. ነጻ ሚድያ ናቸው።

እነዚህ ተቋማት በአግባቡ ባልተደራጁበት ሁኔታ ነጻና ፍትሓዊ ምርጫ የማይቻል እንደሆነ የሃገራችን ህዝብ ከሊቅ እስከ ደቂቅ የተረዳው ጉዳይ ሆኗል።

ከምርጫ 97 በኋላ ወያኔ ሲከውነው የከረመው ስራ ግን ምርጫ ነጻና ፍትሓዊ እንዲሆን አስፈላጊ ናቸው የተባሉትን ተቋማት ከመቼውም በከፋ መልኩ በቁጥጥሩ ስር የማስገባት ስራ ነው። የመከላከያ የደህንነትና የፖሊስ ተቋም የመለስ ዜናዊን አምባገነናዊ የግል ፍላጎት ለማስፈጸም በሚያመች መልኩ ተጠናክሮ ተደራጅቷል። ፍርድ ቤቶች የመለስንና የጥቂት ባልደረቦቹን የፖለቲካ ውሳኔ የሚተገብሩ የካድሬ ዳኞች ጋጣ ሆነዋል። የምርጫ ቦርዱም ሙሉ በሙሉ ዛሬም እንደትናንቱ በወያኔ ካድሬዎች እንደተሞላ ነው።

በሃገሪቱ ማቆጥቆጥ ጀምሮ የነበረው የግል ጋዜጦች ነጻነት ከሃገር ጠፍቷል። ወያኔ የሃገሪቱን መገናኛ- ብዙሃን በሞኖፖል ይዞ ህዝብንና ሕጋዊ ተቃዋሚ ብሎ ራሱ ፈቃድ የሰጣቸውን የፖለቲካ ድርጅቶች እያሸበረ ይገኛል። ህዝብ አስተማማኝ መረጃ የሚያገኝባቸውን እንደ የአሜሪካ ድምጽ ሬዲዮና ሌሎችም የመገናኛ ብዙሃን፡ ከፍተኛ ወጪ በማውጣት ማፈን መጀመሩን ያለምንም ሃፍረት የተናገረበት ደረጃ ላይ ደርሷል።

ወያኔ ይህንን ሁሉ የሚያደርገው አምባገነናዊ የሆነ በህዝብ የተተፋ እናሳ ቡድን መሆኑን ስለሚያውቅ ነው። በነጻና ፍትሃዊ ምርጫ በምንም አይነት በስልጣን መቀጠል እንደማይችል ከምርጫ 97 በቂ ተመክሮ ስለቀሰመ ነው።

ስለዚህም ነው የ2002 ምርጫ እውነተኛ ምርጫ ሳይሆን መለስ ዜናዊና የግፍና የዘረፋ ሸሪኮቹ በምርጫ 1997 ተሸንፈው፡ ነገር ግን ህገ ወጥ በመሆን መንገድ የህዝብን ድምጽ ነጥቀው የያዙትን የመንግስት ስልጣን ህጋዊ ለማደረግ የተቀነባበረ ድራማ ነው የምንለው።

አምባገነኑና እናሳው የወያኔ አገዛዝ ከ1997 ምርጫ ውርደት ተምሮ የ2002ቱን ምርጫ አስቀድሞ በመስረቅ አሸናፊነቱን በእጁ ይዞ ተቀምጧል። ህዝብ እንዲመርጥ ተቃዋሚዎችም ውድድር እንዲገቡ የሚፈልገው በስርቆት በእጁ የያዘውን የምርጫ ውጤት ዴሞክራሲዊና ህጋዊ ቅብ እንዲቀቡለት ብቻ ነው። እንዲህ ዓይነቱን በዴሞክራሲ ስም በወያኔ የሚፈጸም ሸፍጥ መቃወም፡ ማውገዝና ሸፍጡ እንዳይሳካ ማድረግ ከሁሉም ለዴሞክራሲ ለሰላም ለነጻነት፡ ለእኩልነትና ለህጋዊነት ከቆሙ የፖለቲካ ድርጅቶችና ቡድኖች የሚጠበቅ ታሪካዊ ግዴታ ነው።

ነጻና ፍትሓዊ ምርጫ የሃገራችንን የተወሳሰቡ ችግሮች መፍቻ ዋንኛው መሳሪያ ነው ብለን እናምናለን። ነገር ግን እንዲህ ዓይነቱ ነጻና ፍትሓዊ ምርጫ የሚደረገውና ህዝብ በዴሞክራሲዊ ምርጫ የሰየመው መንግስታዊ ስርዓት የሚቋቋመው ወያኔ በየግዜው በሚያዘጋጀው የፌዝ ምርጫ በመሳተፍ አይደለም።

እንዲህ ዓይነቱ ተሳትፎ በዴሞክራሲና በምርጫ ስም የጥቂት አምባገነኖች እጅ ከማጠናከር የተለየ ትርጉም አይኖረውም።

በሃገራችን ነጻ ምርጫ እንዲደረግ ዴሞክራሲ፡ ፍትሕ፡ እኩልነት፡ ነጻነትና ሰላም እንዲሰፍን የምንፈልግ ከሆነ በሃገሪቱ ሰላማዊና ዴሞክራሲዊ የስልጣን ሽግግር እንዳይኖር በእብሪት መንገዱን

የዘጋውን የወያኔ አናሳ ቡድን ከኢትዮጵያ ህዝብ ጫንቃ ላይ ማስወገድ ብቻ ነው። ይህንን ለማከናወን የኢትዮጵያ ህዝብና የህዝቡን እውነተኛ ጥቅምና ፍላጎት የሚያስቀድሙ የፖለቲካ ድርጅቶች ቅድሚያ ሊሰጡት የሚገባው አስቀድሞ ውጤቱ በታወቀ ምርጫ መሳተፍን አይደለም።

በጋራ በመተባበርና ሁሉንም አይነት የትግል ስልት በመጠቀም የዴሞክራሲ ጸር የሆነውን የወያኔን ህገወጥና አምባገነናዊ አገዛዝ ከኢትዮጵየ ምድር ለመጥረግ ቆርጠው በመነሳት ብቻ ነው።

ይህ የጋራ መግለጫ ምርጫ 2002ን በሚመለከት በመግለጫው የተካተቱት ድርጅቶች አቋም መግለጫ ብቻ አይደለም። የወያኔ አምባገነናዊ አመራር በተባበረና በተቀናጀ መልኩ አብረን ለመታገል መቁረጣችንን እና፣ ሌሎችንም የፖለቲካ ድርጅቶችና የኢትዮጵያ ህዝብ አማራጭ ለሌውና ለማይቀረው መራራ ትግል በጋራ አብረውን እንዲነሱ ጥሪ የምናቀርብበትም ነው።

ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ

1. የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር ( ኢ.ህ. አ.ግ )
2. የቤንሻንጉል ህዝብ ንቅናቄ ( ቤ.ህ.ነ.ን )
3. የትግራይ ህዝብ ዴሞክራስያዊ ንቅናቄ ( ዴ.ም.ህ.ት )
4. የአማራ ዴሞክራስያዊ ሃይል ንቅናቄ ( አማራ. ዴ.ሃ.ን )
5. ግንቦት -7 ለፍትህና ለእኩልነት ሃይል ንቅናቄ ( ግንቦት -7 )
6. የኢትዮጵያ ህዝቦች የፍትህና እኩልነት ግንባር ( ፍ.እ.ግ )
7. የዓፋር ህዝብ ፓርቲ
8. የጋምቤላ ህዝብ ነጻነት ንቅናቄ
9. የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት የፍትህ ንቅናቄ